# የወያኔን ስሕተትና ወንጀል ሌላው ኃይል ሲፈጽመው ትክክልና ሕጋዊ ሊሆን አይችልም!

በተደጋጋሚ ጊዜያት በተለያዩ የመወያያ መድረኮች ላይ ሲነገር የምሰማውና በውስጤም ትልቅ ጥያቄ የጫረብኝ ጉዳይ አለ። ይህውም ወያኔን ብቸኛ የኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያዊያን ጠላት አርጎ በማስቀመጥ ሌሎች ኃይሎች ወይም ግለሰቦች ያሻቸውን ቢያደርጉ፣ ሕግ ቢተላለፉ፣ በጎጥና በዘር ፖለቲካ ውስጥ ተዘፍቀው ሕዝባቸውን ቢያዋርዱ፣ መብት ቢጥሱ፣ የሰዎችን ክብር እና ስብዕና የሚያዋርዱ ተግባራትን ቢፈጽሙ፣ ከዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብና መርሆዎች እርቀው ፈላጭ ቆራጭ ቢሆኑ፣ ወያኔ የተጓዘበትን ሕዝብን፣ አገርን እና ኢትዮጵያዊነትን የመካድ መሰሪ ተግባር ሲደግሙትና ተያይዘውም ቁልቁል ሲወርዱ ብናይ እንኳን ወያኔን አሽቀንጥሮ ለመጣል በሚደረገው ትግል ወስጥ እነዚህ ኃይሎች ግንባር ቀደም ተሳታፊ እስከሆኑ ድረስ ወይም ሥርዓቱን እስከተቃወሙና እስካወገዙ ድረስ ሊተቹ፣ ሊወገዙ ወይም ሊሚያደርሷቸውም ጥፋቶች ተጥያቂ ሊደረጉ አይገባም ከሚል እምነት የመነጨ ውይም "የጠላቱ ጠላት ወዳጄ" አይነት አስተሳሰብ በብዙ ሥፍራዎች ላይ ለነፃነት እንታገላለን በሚሉ ኃይሎች ሲነገር አስተውያለሁ።

ይህ አይነቱ የተወላገደና መርህ የለሽ አስተሳሰብ እየጠነከረ ከመምጣቱም የተነሳ ከፖለቲካ ድርጅቶችና ካድሬዎቻቸው አልፎ ለሰብአዊ መብቶች መከበር እና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እንታገላለን በሚሉ ግለሰቦች፣ የመገናኛ ሚዲያዎች (የቴሌቪዥን እና እሬዲዮ ጣቢያዎችን ጨምሮ የተለያዩ የዜና ማሰራጫ ድህረ-ገጾች)፣ የሲቪክ ማኅበራትና የተለያዩ ቡድኖች ዘንድም እንደ ወረርሽኝ እየተንሰራፋ መጥቷል። በአገር ጉዳይ የምናበረክተው አስተዋጸኦ የኢትዮጵያን ሕዝብ የራሱ ሥልጣን ባለቤት ለማድረግ ከሆነ እና ሰብአዊ መብቶች የተከበሩባት፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የተገነባባት፣ የሕግ ልዕልና እና የሕግ የበላያነት የተረጋገጠባት ኢትዮጵያ እንድትኖረን ከሆነ በምን መስፈርት ነው አንዱን ጎሣኛ እያወገዝን ሌላኛውን ጎሣኛ የምናጠበድለው? አንዱን አገር ገንጣይ አይንህን ላፈር እያልን ሌላኛውን አገር በማስገንጠል የፖለቲካ ስካርና ምኞት የሚናውዘውን እሹሩሩ የምንለው? አንዱን በወንጀለኛነት እና በሰብአዊ መብቶች እረጋጭነት እየኮነንን ያንኑ ድርጊት የሚፈጽሙ ሌሎች ኃይሎችን ለዴሞክራሲያዊ ለውጥ ኢጋር የምናደርገው?

ይህን አስተያየት እንድሰጥ ምክንያት ወደሆነኝ ፍሬ ጉዳይ ልመለስና ፐ/ር መስፍን ወልደማሪያም ክፍል አንድ ብለው የጀመሩት ዳሰሳ እራሳችንን ለመፈተሽ እና ከስህተታችንም ለመታረም ድፍረቱ ካለን ብዙ ልንማርበት የሚገባ ቁምነገሮችን የያዘ ነው። ምንም እንኳን ፐ/ር መስፍን የኢሳትን ገለልተኝነትና ነጻ ሚዲያነት በተመለከተ በመጀመሪያዎቹ ክፍሎች ውስጥ በጻፉዋቸው ሃሳቦች እና ባንጸባረቁት አቋም ባልስማማም ይህን ጉዳይ በማንሳት ለውይይት በር በመክፈታቸው ላመሰግን እወዳለሁ። በመጀመሪያ ኢሳት እያበረከተ ያለውን አስተዋጸኦ ለማኮሰስም ሆነ አሳንሼ ለማቅረብ አልወድም። ኢሳት መረጃዎችን በማሰራጨት እረገድ ቀላል የማይባል ሚና እየተጫወተ መሆኑ ግልጽ ነው። ይሁንና ሚዲያውም ሆነ ሁሉም ሳይሆኑ የተወሰኑት በዙሪያው የተሰበሰቡ ግለሰቦች ከላይ ከጠቀስኩት ወያኔን ብቻ ኢላማ ያደረገና ሌላው "እንዳሻው" የሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ ሰለባዎች መሆናቸውን የሚያመላክቱ በርካታ ዘገባዎችን ሲያስተላልፉ ማየት የተለመደ ሆኗል። ይህ ያለመወቀስ፣ ያለመተቸትና ያለመገምገም ከለላ የተሰጣቸው የፖለቲካ ኃይሎች ባልተመጣጠነ መልኩም ቢሆን በኢሳት የአየር ጊዜ ማግኘታቸውና ኢሳትም ወያኔን ከጠዋት እስከ ማታ ሲያወግዝ ውሎ ማምሸቱ ቀንደኛ የወያኔ ተቃዋሚ መሆኑን እና ለተቃዋሚዎችም የመተንፈሻ መድረክ መሆኑን ያሳያል እንጂ ለገለልተኛና ነጻ ሚዲያነቱ መገለጫ ሊሆነው አይችልም።

ፕ/ር መስፍን እንዳሉት በኢሳት ላይ የተለያዩ አስተሳሰቦችን ያነገቡ ኃይሎች በተናጠል እንጂ እርስ በርስ ሲሟገቱ እና ክርክር ሲያደርጉ አለመስተዋሉ አንድ ድክመት ቢሆንም ምንጩ ግን ከላይ የጠቀስኩት የአስተሳሰብ ችግር ይመስለኛል። ኢሳት ሌሎች የፖለቲካ ኃይሎችን ሲገመግም፣ ስህተቶቻቸውን ሲነቅፍ ወይም ላጠፉቻቸው ጥፋቶች ተጠያቂዎች ሲያደርግ ያየሁበት አጋጣሚ ትዝ አይለኝም። ለሕዝብ አደባባይ የወጡና መወያያ በሆኑ የተቃዋሚ ኃይሎች ገበና ላይ ጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና አልፎ አልፎ በሚያደርጋቸው ውይይቶች ከሚያነሳቸ ጥያቄዎች ውጪ ኢሳት 'አይኔን ግንባር ያድርገው' በሚል አንዳልሰማ ነገሮችን ሲያልፍ ወይም ሲሸፋፍን ማየት የተለመደ ነው። በተለየ ሁኔታም በግንቦት 7 እና ከኤርትራ መንግስት ጋር የተያያዙ ማናቸውንም ጉዳዮች፣ አስተያየቶችን ሆነ ቅሬታዎችን ለማስተናገድ ኢሳት ገና ድፍረቱን አላገኘም ወይም ነጻነቱ የለውም ወይም ከመነሻውም የተፈጠረው ይህንኑ ባህሪ ይዞ እንዲቀጥል ነው።

ቅድም ያነሳሁት የመርህ ጉዳይ ለኢሳት የሚኖረው ትርጉም ለኔ ግልጽ አይደለም። አንድ ኢትዮጵያዊ በወያኔ መንግስት በደል ሲፈጸምበት ኢሳት በማጋለጡም ሆነ ተጠያቂ በማድረጉ እረገድ የሚያሳየው ትጋት ይበል የሚያሰኘውን ያህል ያንኑ ድርጊት በአንድ ኢትዮጵያዊ ላይ ሻቢያ ወይም በተቃዋሚ ጎራ ከተሰለፉት አንዱ ኃይል ሲሆን ኢሳትን የማይነዝረው ከሆነ ነገር አለ ማለት ነው! ለዚህ ወደፊት በምጽፋቸው ጽሑፎች ላይ ማስረጃዎችን እያጣቀስኩኝ ለማሳየት እሞክራለሁ። ለማንሳት የምፈልገው ቁምነገር ግን አንድ ለሰብአዊ መብቶች መከበር እቆረቆራለሁ የሚል ግለሰብ ወይም ቡድን ወይም እንደ ኢሳት ያለ ሚዲያ ጥሰቱ በማንም ላይ ይፈጸም፣ በየትም ሥፍራ ይፈጸም፣ በማንም ይፈጸም ተቆርቋሪነቱን እና ድምጹን እኩል ሊያስተጋባ ይገባዋል። ይህ ካልሆነ ገለልተኝነት፣ መርህ፣ ነጻነት፣ ፍትሕ እና ለሕዝብ ተቆርቋሪነት ጥያቄ ውስጥ ይወድቃሉ።

አንድ የመጨረሻ ነጥብ ላክልና አስተያየቴን ልቋጭ። ሌላው ትዝብቴ በአደባባይ የሕዝብ በሆኑ እና አገራዊ ጉዳዮች ላይ ያሻንን ለመናገር፣ ለመተንተን፣ አቋማችንን ለመግለጽ፣ ሌሎችንም ለመወንጀልና ለመተቸት ያለንን ድፍረት ያህል አስተያየቶችን ለመቀበል፣ ባደባባይ ለመተቸትና ለመወቀስ ድፍረት የማጣታችን ጉዳይ ነው። በርካታ ግለሰቦች፣ ቡድኖች እና የፖለቲካ ድርጅቶች የሕዝብ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ያገባኛል በሚል የባለቤትነት ስሜት በማንኛውም መልኩ ይሁን ደረጃ የሃሳብ ወይም የተግባር ተሳትፎ ማድረጋቸው የሚደገፍ ተግባር ነው። ይሁንና አደባባይ እራስን ካወጡ በኋላ እኔን በተመለከተ ሃሳብ አትስጡ፣ አትተቹኝ፣ አትውቀሱኝ የሚባል ፈሊጥ ጥሩ መከላከያ አይሆንም። “ቀድሞ ነበር እንጂ መጥኖ መደቆስ አሁን ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ” ነው የሚሆነው። ከግል ሕይወታችን አልፈን አደባባይ ስንወጣና በተለይም በሕዝብ ጉዳይ ውስጥ ገብተን ተሳታፊ መሆን ስንጀምር ሃሳባችን ብቻ ሳይሆን እኛነታችንም የሕዝብ ይሆናል። ሕዝብ ደግሞ የራሱ በሆነ ጉዳይ ላይ ያሻውን የመምከር፣ የማንሳትና የመጣል ሙሉ መብት አለው። ይህን ሃሳብ ያካተትኩት ከኔ ቀደም ብሎ “አንድነት” በሚል መጠሪያ በፕ/ር መስፍን ላይ ለምን ኢሳትን እና ተቃዋሚዎችን ተቹ በሚል ለሰነዘሩት አመክንዮ የጎደለው ወቀሳ ምላሽ ቢሆን በሚል ነው።

እድሜና የተሟላ ጤንነትን ለማከብርዎ ፕ/ር መስፍን ወልደማሪያም እመኛለሁ!!

ከቀደሙት የምንማርበት ልቦና ይስጠን!

ያሬድ ኃይለማርያም

ከቤልጅየም